በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-210953

29/03/2014ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1ኛ. አቶ አርአያ ዮሴፍ -ቀረቡ

2ኛ. አቶ ፈቀደ ዮሴፍ - -አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ወ/ሮ አስናቀች መንግስቴ - አልቀረቡም

2ኛ. ወ/ሮ ብዙ ደበሌ - ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

# ፍርድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች በቀን 09/11/2013 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.376953 በቀን 8/11/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ሰሚው ችሎት እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ሲሆን አመልካቾች በአለልቱ ወረዳ ፍርድ ቤት ተከሳሾች የነበሩ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብ ነበሩ፡፡

የአሁን 1ኛ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በአመልካቾች ላይ አሻሽለው ባቀረቡት ክስ አመልካቾች በጋራ በመሆን በ2009 ዓ.ም ምንም መብት ሳይኖርቸው ከሚበቃ ከተማ ቀበሌ 01 ፍትሕ ጽ/ቤት አካባቢ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተብሎ በሚጠራው ቦታ የሚገኘውን 600 ካ.ሜ የሆነ 39 ቅጠል ቆርቆሮ በላዩ ላይ ያለውን ግምቱ ብር 200,000.00/ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ሊያወጣ የሚችል እና አወሳኙ በክስ ዝርዝር የተገለፀው በ1984 ዓ.ም እናቴ ወ/ሮ መንግስቴ ደስታ የምትባል የተናዘዘችልኝ ይዞታ በዚሁ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.12873 በቀን 06/05/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት በዚህ ይዞታ ላይ ወራሽነትን አረጋግጬ ወንድሞቼ የሆኑትን ጣልቃ ገቦችን ውስጥ ትቼ በስራ ምክንያት ወደ አዲስ አበባ ከተማ ከሄድኩ በኋላ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ በስራ ምክንያት ወደ አረብ ሀገር በመሄዱ ምክንያት  በሕገ ወጥ መንገድ ይዘውብኝ ቤት ሰርተውበት እየነገዱበት ስለሆነ በራሳቸው ወጪ የሰሩትን ቤት አፍርሰው ይዞታውን እንዲለቁልኝ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

የአሁን አመልካቾች በሰጡት መልስም የአሁን 1ኛ ተጠሪ ተደረገልኝ የምትለው ኑዛዜ ላይ የቤት ቁጥር የቤት ቁጥር የለውም፣ ካሬ ሜትርም የለውም፣ አዋሳኝም የለውም፣ ቤቱ ስንት ቅጠል ቆርቆሮ እንደሆነም አይገልጽም፣ ስለሆነም የአሁን 1ኛ ተጠሪ ጠቅሳ ያቀረበችው ቤት የቀበሌ ሆኖ ለጊዜው እንዲያርፉበት የተደረገ ነው ስለሆነም 1ኛ ተጠሪ በዚህ ይዞታ ላይ የባለይዞታነት ማስረጃ ስለሌላት ልትጠይቀን አትችልም፡፡እኛ በማይክሮ እና በጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ ተደራጅተን መኖሪያ ቤታችንን ብር 200,000.00 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ የሚያወጣ የሰራንበት እና በብሎኬት ምርት እና ስራ  ደብሊዩ/ኬ/ቲ/አይ/ቲ በቀን 23/04/2007 ማስረጃ አውጥተንበት እየሰራንበት ስለሆነ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ክስ ውድቅ እንዲሆንልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

የአለልቱ ወረዳ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቶና ተገቢውን ማጣራት አድርጎ በሰጠው ውሳኔም ተጠሪዎች ለይዞታው ማስረጃ የሌላቸው መሆኑንና ግብርም ያልገበሩበት በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎት ይህ ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፀና ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻር የቤት ቁጥር 39 የሆነው ቤት በማን ስም እንዳለ በማጣራት ከሰው ምስክሮቹ ቃልና ከኮሚቴ ሪፖርቱ ጋር በመመዘን ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን መልሶታል፡፡

በዚህ አግባብም የአለልቱ ወረዳ ፍርድ ቤት ባደረገው ማጣራት የሚቃዋ ፊቼ ገሊላ ከተማ አስተዳደር ቤቱ በማን ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ ማስረጃ የሌለው መሆኑን መግለፁን፤ከዚህ ባለፈ የሽማግሌዎችን ቃል በመቀበል ያቀረበው ሪፖርት ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፤የግራ ቀኙ ምስክሮች የሰጡት ቃል ተመጣጣኝ መሆኑን፤የወራሽነት ማስረጃን በተመለከተ 1ኛ ተጠሪ መብት ከሌላቸው ውድቅ ሊደረግና ዋጋ ሊያጣ የሚችል መሆኑን፤ኑዛዜው ስለይዞታው ምንም የማይል ቤቱ የት እንደሚገኝና አዋሳኙ እነማን እንደሆኑ የማያመለክት መሆኑን፤አመልካቾች ያቀረቡት ህዳር 19 ቀን 1983 ዓም የተፃፈው ውል አዋሳኙ ሙሉ ለሙሉ ባይመሳሰልም ግንኙነት ያለው መሆኑን፤በይዞታው ላይ ማንም ግብር የማይከፍልበት መሆኑን፤ተጠሪዎች ያቀረቧቸው ምስክሮች የባለይዞታ የምስክር ወረቀትን ለመደገፍ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሚረዱ እንጂ በራሳቸው ባለቤትነትን ለማሳየት በቂ አለመሆኑን በመጥቀስ የቀረበው ክስ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 33(2) እና (3) መሰረት ውድቅ ነው በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች የአለልቱ ወረደ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታ ለሰሜን ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ፍርድ ቤቱ በሰጠው ውሳኔም የተጠሪዎች ምስክሮች በአከራካሪው ቦታ ላይ ያለው አሮጌ ቤት የ1ኛ ተጠሪ እናት መሆኑን፤ይህንን ቤትም 1ኛ ተጠሪ በውርስ ያገኙ መሆኑን በቦታው ላይ አሁን የተሰራው ቤት ሁለት አመት የማይሞላው መሆኑን ያስረዱ መሆኑን፤የተለያዩ አካላት የአካባቢውን ሽማግሌዎች በመያዝ ባደረጉት ማጣራት ይዞታው የወ/ሮ መንግስቴ ደስታ መሆኑን ፤አመልካቾች በሽያጭ አስተላልፎልናል የሚሉት ህምሳ አለቃ ገ/ማሪያም ጉደታ በይዞታው ላይ መብት የሌለው መሆኑን ማረጋገጣቸውን በመጥቀስ በማስረጃ ምዘና ረገድ ተጠሪዎች በይዞታው ላይ የተሻለ መብት ያላቸው መሆኑን ማስረዳታቸውን በመጥቀስ አመልካቾች መብት በሌላቸው መሬት ላይ ያከናወኑት ግንባታ በራሳቸው ወጪ በማፍረስ ይዞታውን ለአሁን ተጠሪዎች እንዲለቁ በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ሽሯል፡፡

የአሁን አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኙን በፍ/ስ/ስ/ ሕግ ቁጥር.337 መሰረት የሰረዘው ሲሆን ሰበር ሰሚ ችሎቱም በስር ፍርድ ቤቶች የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት አመልካቾች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም በአጭሩ የአለልቱ ወረዳ ፍርድ ቤት ከዚህ በፊት ለክርክር መነሻ የሆነውን ቤት የማን እንደሆነ፤ በማን ስም ተመዝግቦ እንዳለ እንዲሁም ማን ግብር እንደሚገብርበት ተጣርቶ እንዲቀርብ በታዘዘው መሰረት በዚህ አከራካሪ በሆነው እና ክርክር ባስነሳው ቦታ ላይ ማንም መብት እንደሌለው፤ እንዲሁም ማንም ግብር የገበረበት እንደሌለ፤ የሚቃዋ ፍቼ ገሊላ ከተማ አስተዳደር በደብዳቤ ቁጥር G/9/B/M/M/F/G 1113/64 በቀን 03/10/2011 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ለወረዳው ፍርድ ቤት ገልጿል፡፡ይህም ተጠሪዎች ከመነሻውም አመልካቾች ላይ መብት በሌላቸው ጉዳይ ላይ ክስ ማቅረባቸውን ፤ክስ ባቀረቡበት ጉዳይም የመክሰስ መብት የሌላቸው መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ እያለ በዚህ አግባብም የወረዳው ፍርድ ቤት ሕጉን በተከተለ መልኩ የአሁን 1ኛ ተጠሪ በይዞታው ላይ ምንም መብት የላትም ብሎ ክሱን ውድቅ ማድረጉ በአግባቡ ሆኖ እያለ በየደረጃው ያሉት የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የአሁን ተጠሪዎች ባለመብት ናቸው ብለው መወሰናቸው አግባብነት የለውም፡፡የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተፈፀመውን የሕግ ስሕተት ሊያርም ሲገባው የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ማጽናቱ አግባብነት የለውም፡፡ስለሆነም የስር የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተሽሮልን ተገቢው ፍርድ እንዲሰጥልን በማለት አመልክተዋል፡፡

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታና ቤት የተጠሪዎች አውራሽ ይዞታ ስለመሆኑ የሰነድ ማስረጃ ባላቀረቡበት እና የሚመለከተው የአስተዳደር አካል ተጠይቆ ቤትና ይዞታው የተጠሪዎች አውራሽ አለመሆኑን ምላሽ በቀረበበት የስር ፍርድ ቤት አመልካቾች የሰሩትን ቤት አፍርሰው ይልቀቁ በማለት የወሰነበትን አግባብነት ከፍ/ስ/ስ/ ሕግ ቁጥር 33(2)(3) አኳያ ለመመርመር የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

ተጠሪዎች በሰጡት መልስም የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.81912 ላይ ግንቦት 17 ቀን 2013 ዓ.ም ለወሰነው ውሳኔ፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 344570 ላይ ሐምሌ 1 ቀን 2013 ዓ.ም ለሰጠው ትዕዛዝ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.376953 ላይ ሐምሌ 08 ቀን 2013 ዓ.ም ለሰጠው ትዕዛዝ መሰረቱ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 321496 ላይ የካቲት 17 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ነው፡፡ይዞታው የማነው የሚለውን በተመለከተ በግራ ቀኝ የቀረበ የሰነድ ማስረጃ ያልቀረበ ስለሆነ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ የማነው የሚለውን ጭብጥ የምስክሮችን ቃል እና ከከተማ አስተዳደሩ የቀረበውን ቃለ ጉባኤ በመመዘን ውሳኔ እንዲሰጥ ትዕዛዝ የሰጠው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው፡፡የሰሜን ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረት በማድረግ ማስረጃን ለመመዘን ባለው ስልጣን የምስክሮችን ቃል እና የቃለ ጉባኤውን ይዘት በመመዘን ለክርክር መነሻ የሆነው ይዞታ የአሁን ተጠሪዎች አውራሽ የሆኑት የሟች ወ/ሮ መንግስቴ ደስታ መሆኑን አረጋግጦ መወሰኑ እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም በይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በማጽናት መወሰናቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የለውም፡፡

አመልካቾች በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 321496 ላይ የካቲት 17 ቀን 2012 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው ውሳኔ አግባብ አልነበረም የሚሉ ከሆነ በወቅቱ ስልጣን ላለው የበላይ ፍርድ ቤት ተፈጥሯል የሚሉትን መሰረታዊ የሕግ ስሕተት በመጥቀስ አቤቱታ ማቅረብ ነበረባቸው እንጂ አሁን በዚህ ደረጃ በስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሰረት ተወስኖ እያለ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል ማለታቸው ራሱ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ነው፡፡ስለሆነም የተፈጠረ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የሌለ በመሆኑ የስር ከፍተኛ፣ ጠቅላይ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የለውም ተብሎ እንዲወሰንልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾችም የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር ክርክሩን ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ፣ከተገቢው ሕግና ከስር ፍርድ ቤት ክርክር አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 80(3)(ሀ) እና በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 10(1) እንደተመለከተው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ውስጥ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞ ሲገኝ በሰበር አይቶ የማረም ነው፡፡በዚህ አግባብም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር ሰሚነት ስልጣኑን ተግባራዊ ሲያደርግ ፍሬ ነገርን በተመለከተ በዋነኝነት መነሻ የሚያደርገው ስልጣን ባላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ነው፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ የስር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአለልቱ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ የሻረው አመልካቾች በ1993 ዓም በተደረገ የሽያጭ ውል አከራካሪውን ቤት በመግዛት ቀድሞ የነበረውን ቤት በማፍረስ አዲስ ቤት መስራታቸውን ካስረዱት የአመልካቾች ምስክሮች ቃል ይልቅ በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ የተደረገው ማጣራት ስለጉዳዩ በጥልቀት የሚያውቁትን የአካባቢውን ሽማግሌዎች በመያዝ የተደረገ ሆኖ ይዞታው የወ/ሮ መንግስቴ ደስታ መሆኑን፤አመልካቾች በሽያጭ አስተላልፎልናል የሚሉት ሀምሳ አለቃ ገ/ማሪያም ጉደታ በይዞታው ላይ መብት የሌለው መሆኑን ማረጋገጣቸውን፤የተጠሪዎች ምስክሮች በአከራካሪው ቦታ ላይ ያለው አሮጌ ቤት የ1ኛ ተጠሪ እናት መሆኑን፤ይህንን ቤትም 1ኛ ተጠሪ በውርስ ያገኙ መሆኑን በቦታው ላይ አሁን የተሰራው ቤት ሁለት አመት የማይሞላው መሆኑን ያስረዱ መሆኑን፤በዚህም ከማስረጃ ምዘና አንፃር ተጠሪዎች በይዞታው ላይ የተሻለ መብት ያላቸው መሆኑን ማስረዳታቸውን በመጥቀስ ነው፡፡ይህ የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ በዚህ ችሎት ሊለወጥ የሚችለው የስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ ምዘና ረገድ የፈፀሙት ስህተት ከተገኘ ብቻ ሲሆን ይህ ችሎት ባደረገው ምርመራ በስር ፍርድ ቤት የተፈፀመ የማስረጃ ምዘና መርህ ጥሰት ያልተገኘ በመሆኑ የአመልካቾችን መከራከሪያ ውድቅ በማድረግ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 81912 ግንቦት 17 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና ይህንን ፍርድ በማፅናት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 344570 ሐምሌ 1 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.376953 ሐምሌ 8 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ትዕዛዝ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር.348(1) መሰረት ፀንተዋል፡፡
2. በሰበር ሰሚው ችሎት ተለዋጭ ትዕዛዝ እስኪደርሰው ድረስ በአለልቱ ወረዳ ፍርድ ቤት አፈፃፀም ምድብ ችሎት በመ/ቁ. 17076 የተጀመረው የአፈፃፀም መዝገብ ለጊዜው ታግዶ እንዲቆይ በቀን 15/11/2013 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

<u>ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡</u>

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሂ/መ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም